# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## የዕለቱ ምስባክ

ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረው ጸሩ
ወይጕይዩ ጸላእቱ እምቅድመ ገጹ
ከመ የሀልቅ ጢስ ከማሁ የሀልቁ

እግዚአብሔር ይነሳ
ጠላቶቹ ይበተኑ
የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ
ጢስ እንደሚበን እንዲሁ ይብነኑ

መዝ ፷፯፤፩-፪

ድህረ ቁርባን ከቅዳሴ ውጭ የሚባል፥

እምሥራቀ ፀሐይ እስከነ አረብ
ይትአኰት ስሙ ለእግዚአብሔር
ልዑል እግዚአብሔር መልእልተ ኵሉ አሕዛብ

ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ
የእግዚአብሔር ስም ይመስገን
እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ያለ ነው

መዝ ፩፻፲፪፤፩-፪

ወንጌል፥ ዮሐ ፳፤፲፱-ፍጻሜ
ቅዳሴ፥ የዲዮስቆሮስ ቅዳሴ (እምቅድመ ዓለም)

## የዕለቱ ትምህርት

### «ሰላም ለእናንተ ይሁን»

ሰላም የውስጥ እረፍት ነው። መድኃኒታችን በትንሣኤው ዕለት እንዲሁም በተገለጠበት ዕለት በዳግም ትንሣኤ ሰላማቸው ለተወሰደባቸው ቤታቸውን ዘግተው ለተቀመጡት ተማሪዎቹ «ሰላም ለእናንተ ይሁን» አላቸው። የተቸነከሩ እጆቹን የተወጋ ጐኑን አሳያቸው። ይህ የሆነው የትንሣኤው ዕለት ሲሆን ቶማስ በዕለቱ ስላልነበረ ደቀ መዛሙርቱ «ጌታን አይተነዋል፤ ከሙታን ተነስቷል» ቢሉት «የችንካሩን ምልክት በእጆቹ ካላየሁ ጣቴን በችንካሩ ምልክት ካላገባሁ እጄንም በጐኑ ካላስገባሁ አላምንም» ብሏቸው ነበር። በዚህ ዕለት ጌታ በዝግ ቤት ገብቶ ቶማስን «የምታምን እንጂ ተጠራጣሪ አትሁን፤ ጣትህን ወደዚህ አምጣና እጆቼን እይ ያመንህ እንጂ ያላመንክ አትሁን» አለው። ቶማስም «ጌታዬን አምላኬ» ብሎ ሃይማኖቱን ገለጠ። ጌታም «ስላየኸኝ አምነሃል፤ ሳያዩኝ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው» አለው። የቶማስን አእምሮም ሰላም ሰጠው፤ ክርስቶስን አምኖ መኖር በራሱ የሰላም ሰው መሆን ነው። ምክንያቱም እርሱ «የሠላም አለቃ ነውና» (ኢሣ ፱፤፮-፯) ሐዋርያውም «የሰላም አምላክ» ይለዋል (ሮሜ ፲፭፤፴፫ ። ሮሜ ፲፮፤፳)።

## ዘመነ ትንሣኤ

ዘመነ ትንሣኤ ወይም ፋሲካ የሚባለው ከጌታችን ትንሳኤ ጀምሮ እስከ ዕርገት ያሉት ቀኖች ናቸው። በእነዚህ ዕለታትና ሳምንታት የሚዘመሩት መዝሙራት ሞትን ትንሣኤን ስቅለትን የመሳሰሉትን የሚያነሱ ናቸው።

በዚህ ዕለት ቤተ ክርስቲያን ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለተማሪዎቹ ሁለተኛ መታየቱን በማስታወስ የነቶማስን ታሪክ እየገለጠች ትሰብካለች።

## የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ይትፌሳህ ሰማይ ወትትሐሰይ ምድር
«ሰማይ ይደሰታል ምድርም ሐሴት ታደርጋለች»

## በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፲፭፤፩-፳ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ፩ኛ ዮሐ ፩፤፩-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፫፤፩-፲ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

ሰላማችን ክርስቶስ በተወለደ ጊዜ የተዘመረውም መዝሙር «ሰላም በምድር» የሚል ነበር (ሉቃ ፪፤፫-፲፬)። የፍጥረት ሁሉ ሰላም ክርስቶስ እሱን በማመን ልቦናችን ይጸና ዘንድ ሲያስተምረን «ልቦናችሁ አይታወክ በእግዚአብሔር እመኑ በእኔ ደግሞ እመኑ» አለ (ዮሐ ፲፬፤፩)። በእርሱም የምናገኘው ሰላም ዓለም ሰላም ከምትለው የተለየ ሰላም መሆኑን «ሰላምን እተውላችኋለሁ ሰላሜን እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ዓለም እንደሚሰጣችሁ አይደለም (ዮሐ ፲፬፤፯) ብሎ አስተማረ ደቀ መዛሙርቱንም ለወንጌል ሲልካቸው «ወደምትገቡበት ቤት ሁሉ አስቀድማችሁ ሰላም ለዚህ ቤት ይሁን በሉ» አላቸው (ሉቃ ፲፤፭-፮)።

ሐዋርያው የክርስቶስ መስቀል የሰላም ምንጭ ስለመሆኑ «በመስቀሉ ሰላምን አደረገ» አለ (ቈላ ፫፤፲፭)። ሐዋርያው አሁንም «የክርስቶስ ሰላም በልባችሁ ይብዛ» ይላል፤ በዚህ ሰላምም እንኖርበት ዘንድ «ቢቻላችሁ በእናንተ በኩል ከሰው ሁሉ ጋር በሰላም ኑሩ» አለ (ሮሜ ፲፪፤፲፰)። በተጨማሪም «እርስ በርሳችሁ በሰላም ሁኑ» ይላል (፩ኛ ተሰ ፭፤፲፫-፲፬)።

አንባቢ ሆይ ሰላምህ ማን ነው?
የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሆነውን ሰላምን በሕይወትህ ይዘኸዋልን? (ገላ ፭፤፳፪) ይህ ሰላም በክርስቶስ ይገኛል (ሮሜ ፭፤፩)፤ የሕይወት ሰላም የሌላቸው ብዙዎች ናቸው። አንተስ ሰላም አለህን? ሰላም ከሌለህ በክርስቶስ ሞትና ትንሣኤ የተገኘውን የክርስቶስን ሰላም በክርስቶስ ያዝ።

«ኦ ንጉሠ ሰላም ኢየሱስ ክርስቶስ ሰላመከ ታበነ»
«የሰላም ንጉሥ ሰላማዊ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ፥ ሰላምህን ስጠን» አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አሜን።